# ቤተሰቦች ልጃቸው አንባቢ እንዲሆን ለማገዝ ሊያደርጉዋቸው የሚችሉ ቀላል ነገሮች

የንባብ ሂደት የሚጀምረው ልጆች በራሳቸው ማንበብ ከመጀመራቸው ከረጅም ጊዜ በፊት ነው። ይህ የመረጃ ወረቀት፤ ቤተሰቦች አብረው በመወያየት፣ በማንበብ፣ በመጫወት እና አዳዲስ ነገሮችን በመዳሰስ የቋንቋ እና የንባብ ክህሎት እድገትን እንዴት መደገፍ እንደሚችሉ የሚያሳዩ ቀላልና በዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ የሚተገበሩ መንገዶችን ያቀርባል፤ ይህም ልጆች ስኬታማ አንባቢዎች ለመሆን የሚያስፈልጋቸውን ክህሎትና በራስ መተማመን እንዲገነቡ ያግዛቸዋል።

---

- በየቀኑ ለልጆችዎ ያንብቡ፤ እንዲሁም ከእነሱ ጋር አብረው ያንብቡ። ልጆችዎ ትምህርት ቤት መሄድ ከመጀመራቸው በፊት ድምፅዎን ከፍ አድርገው ማንበብዎ እጅግ ጠቃሚ ነው። ከእርስዎ ጋር አብረው እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፤ በገጹ ላይ ያሉ ፊደላትን እና ቃላትን እንዲፈልጉ ይጠይቋቸው፤ እንዲሁም ስለ ታሪኩ ከእነሱ ጋር ይወያዩ።.

- ህጻናት ማንበብ ከመማራቸው በፊትም እንኳ ያነጋግሯቸው። አጫጭር እና ቀላል ዓረፍተ ነገሮችን በመጠቀም ቀኑን ሙሉ ከልጆችዎ ጋር ይነጋገሩ። ገና መናገር ከመጀመራቸው በፊትም ከእነሱ ጋር መነጋገርዎ፣ ወደፊት ማንበብ እና መጻፍ ሲማሩ ይረዳቸዋል።

- ልጆችዎ በራሳቸው እንዲያነቡ ያግዟቸው። በቤት ውስጥ ማንበብ ልጆች በትምህርት ቤት የተሻለ ውጤት እንዲያመጡ ይረዳል። በቤትዎ ውስጥ ብዙ የህጻናት መጻሕፍት እንዲኖሩ ያድርጉ፤ እንዲሁም በየሳምንቱ ወደ ቤተ-መጻሕፍት ወይም የመጻሕፍት መደብር ይሂዱ። ልጆችዎ የራሳቸውን የቤተ-መጻሕፍት ካርድ እንዲያገኙ ያግዟቸው እና የሚወዷቸውን መጻሕፍት በራሳቸው እንዲመርጡ ይፍቀዱላቸው።

- ልጅዎ በእድገት ሂደት ላይ መዘግየት ካለበት፣ ማንበብ ለእሱ አስቸጋሪ ወይም ተስፋ አስቆራጭ ሊሆን ይችላል። የማንበብ ክህሎትን ለመደገፍ ቴክኖሎጂን ይጠቀሙ፤ ለምሳሌ በኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ላይ የሚሰሙ መጻሕፍትን መጠቀም፣ ልጅዎት አብሮ እንዲያነቡ እንዲረዳቸዉ መጽሐፍ ሲያነቡ ድምፅዎን መቅረጽ፣ ወይም ቃላቱ ሲነበቡ የሚያሳዩ (highlight)  የሚያደርጉ መተግበሪያዎችን መጠቀም ይችላሉ።.

- ማንበብ አስፈላጊ መሆኑን ልጅዎ እንዲረዳ ያግዙት። ማንበብን እንደ አንድ የመዝናኛ ወይም የመለቀቂያ ጊዜ (free-time) እንቅስቃሴ ይጠቁሙት። ልጆችዎ በቀን ውስጥ ለማንበብ ጊዜ እንዲኖራቸው ያድርጉ። ጋዜጦችን፣ መጽሔቶችን እና መጻሕፍትን በልጅዎ ፊት በማንበብ ጥሩ ምሳሌ ይሁኑላቸው። በኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ላይ እያነበቡ ከሆነ፣ እያነበቡ መሆኑን ልጅዎ እንዲያውቁት ያድርጉ።

- በቤትዎ ውስጥ ለማንበብ የሚሆን ቦታ ያዘጋጁ። ልጆችዎ የሚወዷቸውን መጻሕፍት በቀላሉ ሊያገኟቸው በሚችሉበት ቦታ ያስቀምጡ። ልጆችዎ የተሻለ የማንበብ ችሎታ ሲያዳብሩ፣ ስብስብዎ ውስጥ ይበልጥ ውስብስብ ወይም ፈታኝ የሆኑ መጻሕፍትን ማካተትዎን ያረጋግጡ።

- ለልጆችዎ የመጻፊያ ቁሳቁሶችን ያቅርቡላቸው። ልጆች መጻፍን መማር እና መለማመድ ይፈልጋሉ። ወረቀት፣ እርሳስ፣ እስክሪብቶ ወይም የቀለም እርሳሶችን (crayons) በቤትዎ ውስጥ በማቅረብ እንዲማሩ ያግዟቸው። በፊደል አጻጻፍ ትክክለኛነት ወይም በእጅ ጽሑፍ ውበት ላይ ከመጠን በላይ ከማተኮር ይልቅ፣ የፈጠራ ችሎታቸውን እና ብዙ የመጻፍ ልምዳቸውን ያበረታቱ።

- ከልጆችዎ ጋር በአፍ መፍቻ ቋንቋዎ ያንብቡ እና ይጻፉ። የመጀመሪያ ቋንቋቸውን መለማመድ ልጆችዎ እንግሊዝኛን ማንበብ እና መጻፍ እንዲማሩ ይረዳቸዋል።



©2026 Reading Is Fundamental

# ቤተሰቦች ልጃቸው አንባቢ እንዲሆን ለማገዝ ሊያደርጉዋቸው የሚችሉ ቀላል ነገሮች

Reading Is Fundamental
until every child reads

- ዕለታዊ ተግባራትን አብራችሁ ስትሠሩ ከልጅችዎ ጋር ይነጋገሩ። ልጆችዎን በታ ሲወስዱ፣ ስለሚያደርጓቸው ነገሮች ይነጋገሩ እና ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

- ልጆችዎን በሕይወታቸው ውስጥ የተከሰቱትን ክስተቶች እንዲገልጹ ይጠይቋቸው። ስለ ልምዶቻቸው ማውራት ልጆች ስለእነሱ እንዲያስቡ ይረዳቸዋል። ዝርዝር መግለጫዎችን መስጠት እና የተሟላ ታሪኮችን መናገር ልጆች ስለ ታሪክ አወቃቀር እና ቅደም ተከተል እንዲማሩ ይረዳቸዋል።

- የስክሪን ጊዜን ዋጋ ያለው ያድርጉ። ሁሉም የስክሪን ጊዜ አንድ አይነት አይደለም። በተቻለ መጠን፣ ልጆች ይዘትን በተዘዋዋሪ ከመጠቀም ይልቅ እንዲያስቡ፣ እንዲፈጥሩ፣ እንዲንቀሳቀሱ ወይም ከሌሎች ጋር እንዲገናኙ የሚያበረታቱ ንቁ፣ አሳታፊ ተሞክሮዎችን ይምረጡ። ለዕድሜ ተስማሚ የሆኑ ገደቦችን ያስቀምጡ እና ልጅዎ ምን እያየ ወይም እየተጫወተ እንዳለ በማወቅ ይሳተፉ።

- የልጆችዎን በትምህርት ቤት እድገት ይከታተሉ። ልጆችዎ በትምህርት ቤት እንዴት እየሰሩ እንደሆነ እና ልጆችዎ የተሻሉ ተማሪዎች እንዲሆኑ እንዴት መርዳት እንደሚችሉ ለማወቅ የልጆችዎን ክፍሎች ይጎብኙ። ስለ ትምህርት ቤቱ የንባብ ፕሮግራም እና ልጆችዎ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የት እንደሆነ ይጠይቁ።

ምንጭ፡ የአሜሪካ የንባብ ዘመቻ **(America Reads Challenge)**፣ የአሜሪካ የትምህርት መምሪያ

*ይህ የምክር ጽሑፍ በሌሎች ቋንቋዎችም ይገኛል። በ rif.org ላይ ያገኟቸዋል።



©2026 Reading Is Fundamental

Reading Is Fundamental